# የፓልቶክ ከባድ ሚዛን (Paltalk Heavy Weight)

**ከኢትዮ ዳርጌ**

በአሁኑ ወቅት በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ከሚያደርጉት የርስ በርስ ግንኙነት አንፃር ፓልቶክ ከፍተኛውን አስተዋፅዖ በማድረግ ላይ ይገኛል። የወያኔ ባለሥልጣናት፣ የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች፣ የሕዝባዊ ድርጅት ሐላፊዎች፣ የሃይማኖት አባቶች ሳይቀሩ ያዳምጡታል። ይህንኑ የመገናኛ አዉታር በመጠቀምም ሃሳባቸውን ለሕዝብ ያስተላልፉበታል። ጎረምሳዎችና ኮረዳዎች በምዕራብ ሃገር የደከመ ሰዉነታቸዉን ያዝናኑበታል። በፓልቶክ ከተራ ብልግና አንስቶ ትምህርታዊ ቁም ነገር እስካዘሉት ድረስ ሃሳቦች ይማከሉበታል። የትግል መስክ ተደርጎ እየተወሰደም የማይስማሙ ባለጋራዎች ይሰዳደቡበታል፣ ይፎካከሩበታል፣ ይፋጁበታል፡፡ በፓልቶክ ሁሉንም መስማት የተለመደ ክስተት ሆኗል።

ፓልቶክ ከጥቂት የራሱ የሆነ ፀባይ ማምጣት ጀምሯል። በፓልቶክ መደበኛ ዲስኩረኞች፣ ጋጠ ወጥ ተሳዳቢዎች፣ ሱሰኛ ታዳሚዎች፣ በየክፍሉ ሲመጡ ታዳሚው ኖር ብሎ የሚቀበላቸው ታዋቂ ግለሰቦች ተፈጥረዋል። ጥቂት ዲስኩረኞች በማስተማር ችሎታቸው የታወቁና ብዙ የፖለቲካ ዕውቀት ያዳበሩ በመሆናቸው የሃገሩ ጉዳይ የሚያንገበግበው በሙሉ ተሰብስቦ በፅሞና ይሰማቸዋል። በትምህርት ሰጪነታቸው የሚታወቁት ብዙም ባይሆኑ ውይይት በጦፈበት ክፍል እየተዘዋወሩ ያላቸውን ሃሳብ ሲያካፍሉ ይታያሉ። እነዚህ ግለሰቦች ስለሃገራቸው በየቦታው ሄደው ማስረዳትን የማይታክቱ ሲሆኑ ለፌዝና ለጨዋታ ጊዜ አይባክኑም።

የዚያኑ ያህል ደግሞ በተሳዳቢነታቸው ምክንያት ታዋቂነት ያገኑ ዋልጌዎችም ተፈጥረዋል። በስድብ የሚታወቁት ቀንና ማታ ሳይለዩ ከፓልቶክ የማይጠፉ ሲሆኑ በየሳምንቱ የሚሰድቡትን ግለሰብ ወይም ድርጅት እየቀያየሩ ሲያዋርዱና ሲሳደቡ የሚውሉ ናቸው። እነዚህ ወገኖች በሃገራችንና በማሕበረሰቡ ዘንድ የታወቁ ግለሰቦችን ወይም ድርጅቶችን መወንጀል፣ የራሳቸውን በሳልነት ሊያሳይ ይችላል በሚል ግምት የስድብ ዉርጅብኙን ተያይዘውታል። ተከብረው ሳይሆን ስድባቸው ተፈርቶ ፣ ጠላትነታቸው በመሸሽ ወዳጅነታቸውን መሻት እየተለመደ መጥቷል።

ሌላው ደግሞ በተቃዋሚዎች መካከል ሆነው የተቃዋሚዎችን ክፍፍል እንዲያራግቡ በወያኔ እየተከፋላቸው የሚንቀሳቀሱ ሆዳሞች ቁጥር አነስተኛ አይደለም ። እነዚህ ግለሰቦች በተለያየ ወቅት የማይጣጣም አቋም በማያዝ ሀገሩን የሚወደውን ታዳሚ ያምሱታል። ተስፋ ያስቆርጡታል። በተለይ ከወደአሜሪካ በኩል የወያኔ አምባሳደር የሆነው ታዬ አፅቀ ሥላሴ እየቀጠራቸው የሚንቀሳቀሱት ዛሬ ፓልቶኩን ሞልተውት ይገኛሉ።

በቅርብ ጊዜ አንድ ጓደኛዬ "ዶክተር ኤክስን ታውቀዋለህ?" በማለት ጠየቀኝ።
"አላውቀውም" መለስኩለት።
"እንዴ እንዴት አታውቀውም?"
አንድ ማወቅ የሚገባኝን ግለሰብ የዘነጋሁ መስሎኝ "ምነው ማወቅ ነበረብኝ እንዴ?" ደግሜ ጠየቅሁት።
"አይ እሱን የማያውቀው የለም ብዬ ነው" መለሰልኝ።
"ማነው እሱ? እስቲ ንገረኝ?" ጠየቅሁት።

በድጋሚ "እንዴት እሱን አታውቅም?" በማለት ጀምሮ በመደነቅ እየተመለከተኝ "እሱ እኮ ፓልቶክ ላይ ሂቪ ዌይት (የከባድ ሚዛን) ቡጢኛ ነው" አለና መለሰልኝ።

በጣም ገረመኝ . . . . .ከዚያ በኋላ ነው የፓልቶክ ከባድ ሚዛኖችንም ታዋቂነትን እያፈሩ መምጣታቸውን የተረዳሁት። ይህ በፓልቶክ የመታወቅ አባዜ የተጠናወታቸው ደካሞች በዕውቀታቸው ብዛት ሳይሆን በተሳዳቢነታቸው ለመታወቅ የሚያደርጉት ጥረት ከፍተኛ ነው። የሚናገሩትን በየቀኑ እየቀያየሩ፣ የሚሰድቡትን እየመረጡ የከፈቱት ክፍል እንዲሞላ ይጥራሉ። በምዕራብ ሃገር የእርዳታ ገንዘብ እየኖሩ፣ አንዳንዶቹም በወያኔ ገንዘብ እየተገዙ፣ የሚሰለች ጊዜያቸውን ለማሳለፍ ፓልቶክን እንደ መዝናኛ፣ ወያኔን ከሥልጣን ለማውረድ የሚደረገውን ትግል እንደ የግል መዝናኛ ሥራ (ሆቢ)፣ ከወያኔ የተከፈላቸው ደግሞ ተቃዋሞዎችን ለመከፋፈያ ፓልቶክን ይጠቀሙበታል። ሌሎች ደግሞ ወያኔ ላይ የምር ተቃውሞ ያላቸውን፣ ለመሰረታዊ ለውጥ የሚታገሉ ድርጅቶችን ወይም ግለሰቦችን በመሳደብ ለአገዛዙ እጅ መንሻ ይዘው ይቀርባሉ። ያገራቸውን መሬት ለመመራት፣ ያገራቸውንና የሕዝባቸውን ህልውና መስዋዕት አድርገው ወያኔን እጅ ይነሳሉ።

በዚህ ዘመን መከፋፈል ፋሽን ነው። እንኳን በፖለቲካው፣ በሃይማኖትም ሳይቀር የምናየው ነው። ወያኔ ለ18 ዓመታት ያካሄደው የዘር ፖለቲካ ውጤት ነው። መከፋፈል ሆዳሞች አሜን ብለው የተቀበሉት የወደፊት ሆዳቸውን የሚሞሉበት ተሰፋቸው ነው። መከፋፈል ዘረኞች ወደ ስልጣን መውጫ መረማመጃቸው መሰላል ነው። ፓልቶክ ወያኔ ቅጥረኞቹን በስሙ-ተቃዋሚ በውስጣችን በማስገባት ትግሉ በእሱና በተቃዋሚዎች መካከል መሆኑ ቀርቶ በተቃዋሚው ሜዳ አምጥቶ እርስበርስ ለማናከስ፣ ለማበጣበጥ የሚጠቀምበት አንዱ መንገዱ ነው።

በፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ የሚታየዉ የዉሰጥ መከፋፈል በፓልቶክ ክፍሎችም በከፍተኛ ደረጃ ይንፀባረቃል። አንድ የፓልቶክ ክፍል ለሁለት ይሰነጠቃል። ድርጅት ውስጥ ያልተስማሙ ግለሰቦች ፓልቶክ ላይ መጥተው ልዩነታቸውን ለሕዝብ ለማቅረብ ይጥራሉ፣ ይሰዳደባሉ፣ ይፎካከራሉ። የረባ ልዩነት ይኑራቸውም፣ አይኑራቸውም በፓልቶክ ተከፋፍለው የየበኩላቸዉን ደጋፊ ማሰባሰብ ይጀምራሉ። በራሳቸው የውስጥ አሰራር እዚያው በአባላታቸው መዳኘት ሲገባቸው። ወይም ደግሞ አንዱን የፖለቲካ ድርጅት የሚደግፉ ሦስት አራት ክፍሎች በአንድ ጊዜ ይከፈታሉ። የፖለቲካዉ ድርጅት አመራሮች ክፍሎቹን በማስማማት ፈንታ በየክፍሉ እየሄዱ መግለጫ ይሰጣሉ። መሪዎቹ የየግል ደጋፊያቸውን ያሰባስባሉ። (ለመረጃ ያህል የመኢአድ ደጋፊዎችን ከሶስት በላይ ክፍሎች ውስጥ እርስ በርሳቸው ሲሰዳደቡ ይውላሉ)።

በፓልቶክ ብዙ ሰው ያሰባስብ የነበረው ከረንት አፌርስ የተባለውን ክፍል ወያኔ ብዙ ከጣረ በኋላ ለሁለት ሊከፍለው ችሏል። ይህ በፀረ ወያኔነቱ ይታወቅ የነበረውን ክፍል ለመክፈል በውስጥ ቅራኔዎችን በማራገብ ሆዳም የሆኑ ግለሰቦችን ተጠቅሟል። ወያኔ የገንዘብ ችግር የነበረባቸውን በነዋይ ደጉሟል። ዛሬ የዘር ፖለቲካን ከሥሩ መንግለን እንጣለው የሚሉ እዚው ሲቀሩ፣ ወያኔን እንደጉመውና የክልል ፖለቲካን የላይ ቀለም ቀባብተን እንቀጥል በሚል ስም የወያኔ ሥርጎ ገቦች ዓላማቸውን ለማስፈፀም ከመድረክ ጋር በማበር ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረጉ ነው። እነዚህ መሠረታዊ ለውጥን የማይደግፉ ግለሰቦች ቃሌ የሚል ክፍል ከፍተዋል። በዚህ ቃሌ የሚባል ክፍል ውስጥ ደግሞ የወያኔ የፓልቶክ ወታደሮች ተሰግስገው ከፍፍሉን ያዳምቃሉ። ይህንን ክፍል የሚመሩ የመድረክ አባል የሆኑና በቀድሞ ወያኔ አባልነታቸው የሚታወቁ ናቸው።

እነዚህ ሁለት ክፍሎች አንድ ላይ በነበሩበት ወቅት በአደረጉት ተጋድሎ የተፍረከረከው ወያኔንን ጥለው በወጡ የወያኔ አባላት ምክንያት ብቻ ነው ክፍፍሉ? መድረክ ኢትዮጵያን ከማስማማት መከፋፈል ስለመረጠ ነው አባሎቹን በዚህ ክፍል በመሰግሰግ ለክፍፍሉ ጥረት ያደረገው ? መድረክ በለስ ቀንቶት ስልጣን ላይ ቢወጣ የሚጠብቀን ያው ክፍፍልና የዘር ፖለቲካ ነው? በአሁኑ ጊዜ ለዚህ ክፍል ክፍፍል ጥረት ያደረጉ የመድረክ ከፍተኛ ባለሥልጣናት (ብዙዎቹ የቃሌ ክፍል አጋፋሪዎች ማለትም አድሚኖች ስልጣን ላይ ቢወጡ በዘር ሃገራችንን ላለመከፋፈላቸው ምን መተማመኛ ይኖረናል?

ከሁሉም የባሰው ደግሞ ፓልቶክ ለሁለት ሲከፈል ከዚያ ቀደም የነበረውን ሥም ላለመልቀቅ የሚደረግው ፉክቻ ነው። አንዲት ፊደል በመጨመር ወይም በማጉደል አዲስ ክፍል ከፍተው እኛ ነን ዋነኞቹ ብለው የሚጀምሩ ሞልተዋል። በተለይ ከሁለት አመት በፊት ከኢሕአፓ አፈንግጠው ዴሞክራቲክ ነን ብለው አዲስ ድርጅትና የፓልቶክ ክፍል ያቋቋሙት በፖልቶክ እንኳ መቻቻል አቅቷቸው አንዱ ክፍል እንደተለመደው ሌላውን ክፍል ጥሎ (walkout) ወጥተው VEDR በሚለው ላይ Aberash Berta የሚል ቅጥያ ይዘው ብቅ ብለዋል። ይህ በስም ላይ ድሪቶ የመቀጠል አባዜ ኢሕአፓ ላይ ዴ በመጨመር የተጀመረ ሲሆን በፓልቶክ ላይ መቀጠሉ ደግሞ በጣም የሚያስገርመኝ ነው። ኢሕአፓ የሚለውን ስም አንለቅም፣ ብዙ ዓመት ታግለንበታል ሊሉ ይችሉ ይሆናል። የፓልቶክ ክፍልን በምን ታሪካዊ ገድሉ ነው ስሙ ተከብሮ ድሪቶ የሚጣፍለት? መልሱን ከክፍሉ አላፊዎች ማግኘት ያሻል።

የፓልቶክ ክፍፍል የተለመደ ሂደት ቢሆንም ከ35 ዓመት በላይ ልምድ አለን የሚሉት፣ ከኢሕአፓ የወጡት አንጃ ግለሰቦች የከፈቱት ክፍል ለሁለት ተከፍሎ መታየቱ ብዙውን የፓልቶክ ታዳሚ ገርሞታል። ምንክንያቱን እኔ በግሌ በውል አልወቀው እንጂ (መቼም ወደፊት መሰማቱ አይቀርም) በምክንያት እንደተከፋፈሉ እርግጥ ነው። ከሚጋብዙት እንግዳ፣ ከሚያቀነቅኑት የፖለቲካ አቋም አንፃር ግን በሁለቱም የፖለቶክ ክፍሎች አቋም ልዩነት የለም። አንድ ሊኖር የሚችለው ከድረ ገፆች እንዳነበብኩት በዶክተር ጌታቸው በጋሻውና በመርሻ ዮሴፍ መካከል ያለው የስልጣን ርኩቻ ብቻ ነው። የ35 ዓመት የትግል ልምድ በየፓልቶኩ ሲንዛረጥ ማየት እንዴት ያሳፍራል? በፓልቶክ ክፍላቸዉ ሆ የሚል በርካታ ታዳሚ በመሰብሰባቸው ወያኔንን መጣል ይቻላል ብለው ያምኑ ይሆን? መልሱን ለክፍሎቹ እተወዋለሁ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ እጅጉኑ የሚኮራባቸውን አያሌ ወጣቶች በትግል ሜዳ ካጣዉ ድርጅት “በአካል እንጂ በዓላማ“ ጨርሶዉኑ አልተለየንም ብለዉ የሚምሉት ተነጣይ ወገኖች፣ የሰማዕታት ጉዋዶቻቸዉን አርማ አንስተዉ መታገል ሲኖርባቸው በዘመኑ የክፍፍል ዘይቤ ተዘፍቀው፣ በፓልቶክ ተዋቂ እንግዳ በመጋበዝ፣ ክፍላቸውን ከአፍ እስከ ገደቡ ሞልተው፣ አንዱ ሌላውን የተለየውን ክፍል እንደ ጠላት በመመደብ፣ በታዳሚ ብዛት ክፍሉን ለማሸነፍ የሚያደርጉትን ጥረት ስመለከት እነዚህ ግለሰቦች ምንያህል እንደነቀዙ መገመት አያዳግትም። በእውነት ለዚህ ዓይነት ትግል ነበር ብዙሃኑ አባላት ከቀጠሉት ጉባዔ ረግጠው የወጡት? ብዬ ለመጠየቅም እገደዳለሁ። በተለይ በውስጣቸው ያለው መከፋፈል ጎልቶ ይወጣል ብለው በመፍራት፣ እንግዳን መጥራት እንጂ የፖለቲካ ውይይትን ከማድረግ ተቆጥበው፣ እንግዳ ከሌለ ክፍላቸውን መዝጋትን መምረጣቸውን ስመለከት ራሳቸው በራሳቸው ላይ የመናገር መብታቸውን እንደገፈፉ ስመለከት ሃዘን ይሰማኛል። አቋማቸውን መግለፅ ለምን ይፈራሉ? መልሱን አሁንም ለእነሱ እተወዋለሁ።

በውጭ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ወያኔ ስልጣን ላይ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በፓልቶክ ሳይሆን በነፍስ ያልጠራነው እንግዳ፣ ያላከበርነው መሪ የለም። ታዲያ ያ ብቻ ምን

ጠቀመ? አሁን ምን ተገኝቶ ነው ታዲያ በፓልቶክ በተጋበዘ እንግዳ ብዛት ውድድር የተገጠመው? በዚህ ዓይነትስ ነው ወይ የተሰው ጓዶቻቸንን ዓላማ ግብ የሚያደርሱት? ከኢ.ሕ.አ.ፓ ከወጡ በኋላ ሠራን የሚሉትን ምንድነው? የክፍፍላቸው መነሻ ምክንያት ምንድነው? በፀረ ወያኔ ትግል ውስጥ አቋማቸው ምንድነው? ከአንጃቸው የተባረሩት አባሎቻቸው የተባረሩበትን ምክንያትስ? እነዚህንና ሌሎችንም ጥያቄዎች ለሕዝብ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል። ለሕዝብ ግልጥ የሆነ አሠራር ብዙሃኑ አባላት በቀጠሉት ኢ.ሕ.አ.ፓ ውስጥ የለም ብለው እስከከሰሱ ድረስ የእነሱን ግልጥነት ማሳየት አይኖርባቸውምን?

እኔ በበኩሌ ስንት ወጣቶች የተሰውበት በኢ.ሕ.አ.ፓ ሥም ሲነገድ ማየትን አልፈልግም። በዚህ ይዞታችሁ እንወዳቸዋለን በምትሏቸው በተሰውት ጓዶች ስም ዳግም እያላገጣችሁ መሆኑን አትረዱትም? ዛሬ እያንዳንዱ በቀይ ሽብር የሚወደውን ያጣ ግለሰብ ኢ.ሕ.አ.ፓ ዴ የሚል ድርቶ ተለጥፎ ሲመለከት ልቡ ምን ያህል እንደቆሰለ የተረዳችሁት አልመሰለኝም። ያ ያነሰ ይመስል እንደገና ደግሞ በፓልቶክ ተከፋፍላችሁ የፓልቶክ ከባድ ሚዛን ሆናችሁ ታዋቂ ለመሆን የምትቅበዘበዙት፣ ለግለሰብ ተገዢ ሆናችሁ ለመቅረት መሆኑን በቀደም በድረ-ገጽ ላይ ከተነበበው የደብዳቤ ልውውጣችሁ ተገንዝቤያለሁ። ዛሬ እናመጣዋለን ብላችሁ ጉባዔ ጥላችሁ የወጣችሁበት "የውስጥ ዴሞክራሲ" ምን ያህል እንደሆነ ራሳችሁ በደምብ ታውቂታላችሁና ማስረዳት አልፈልግም። ለመሆኑ ዴሞክራሲው መርኻን ተናገረብን ብላችሁ አባላትን ማባረራችሁ ነው? ትግሬዎች ናችሁ ብላችሁ አባሎችን ለቅማችሁ ስታወጡስ ነውን ?

ከሁሉም የሚገርመኝ ደግሞ የፖለቲካ መሪዎች የፖልቶክ ክፍሎች ሲከፋፈሉ በተከፈሉት ክፍሎች እየሄዱ ቃለ መጠይቅ የሚሰጡት ናቸው። ደጋፊም ተቃዋሚም የሚለየው በዚያ ጊዜ ነው። መከፋፈሉ የሚያስጨፍራቸው የፖለቲካ መሪዎች ሃገራችንን ለማዳን የሚችሉ አይደሉም። ለምን ተከፋፈላችሁ? ብለው አይጠይቁም። ይህንን የሚያሳፍር ተግባር መቼ ነው የምናቆመው? ተከፍለው የሚወጡትን መቼ ነው ማዕቀብ የምናደርግባቸው። ከኢ.ሕ.አ.ፓ ጉባዔ ጥለው ሲወጡ ለምን? ተብለው ቢጠየቁ ኑሮ አሁን በፓልቶክ ባልተከፋፈሉም ነበር። ነገ ደግሞ በግለሰብ ደረጃ ሲበታተኑ ምን ልንል ነው።

መኢአድ በየክፍሉ የተበተኑትን ደጋፊዎቹን ሲሰበስብና እርስ በርሳቸው ማናቆሩን እንዲያቆሙ ሲጥር፣ ሌላው ሌላውም የእርስ በርስ የስልጣን ፍግቻውን ሲያቆም፣ መድረክ በከረት አፌርስ ውስጥ ደጋፊ ተብዬዎቹ የወያኔን የመከፋፈል ዓላማ መፈጸማቸውን ሃይ ሲላቸውና ሲገታቸው ነው ትግሉ ወደ ፊት የሚነጉደው። እኛም ተከታዮቻቸው ግርዱን ከምርቱን እየለየን፣ ለጠላት 'ከፋፍልህ አዳክማቸው' ቆረጣ ቀዳዳ ሳንሰጥ በህብረት ስንቆም። ለእንደዚህ ዓይነት ትግል ነው ቀበቷችንን ጠበቅ ማድረግ ያለብን።

የአንድ የፖለቲካ ድርጅት ትልቅነት የሚለካው ኢትዮጵያውያንን ለመከፋፈል በሚያደርገው ጥረት ወይም በፓልቶክ የራሱን ደጋፊዎች ለማብዛት በሚያደርገው ፉክክር መሆን የለበትም። መሆን ያለበት ለሃገራችን ባለው ራዕይ፣ ኢትዮጵያውያንንም በዚህ ዓላማው ስር በጽናት ለማሰባሰብና አንድ አድርጎ ለማቆም በሚያደርገው እልህ አስጨራሽ ጥረት መሆኑንን መረዳት ይኖርብናል። የትግሉ መንገድ የጠላት አሜኬላ የበዛበት፣ ውጣ ውረዱ ስጋንም ነፍስንም ተፈታታኝ ነውና። ከዚያ በኋላም ነው የፀረ ዘረኝነት ትግሉ መድረሻ ምዕራፉ ላይ የሚደርሰው። አንድ ድርጅት ሕዝብን ማደራጀቱ ነው ትልቅነቱ እንጂ መበተኑ አይደለም መወደስ የሚገባው ጥንካሬው።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !!!